በመንገሻ ዮሐንስ

ከአዲስ አበባ

# ኤርትራ የ21 ዓመታት የጨለማ ጉዞ

የኤርትራ የነፃነት ትግል እ.ኤ.አ ከመስከረም 1961 እስከ ግንቦት29 ቀን 1991 የተካሄደ ሲሆን 30 መራራ የትጥቅ ትግል ዓመታት ሲመራ የነበረውን የአቶ ኢሳያስ ቡድን ነፃነትን በትጥቅ ትግል ከማረጋገጥ ታክቲክ ውጭ የጠራ ፖሊሲ፣ስትራቴጂ እና ፕሮግራም እንዳልነበረው ፣ከዚህ በተጨማሪም ፀረ- ዴሞክራሲ እና ፋሽስታዊ የሆነ አስተሳሰብና ተግባር ይከተል እንደነበር Sallina.com የተሰኘ ድረ -ገፅ ፒሎት በሚል ምስጢራዊ ስም ከሚጠራ የውስጥ አዋቂ እና ነባር ታጋይ ጋር እ.ኤ.አ ሚያዚያ ወር 2012 ያደረገው ቃለ ምልልስ ያስረዳል፡፡የኘው ነባር ታጋይ በቃለ ምልልሱ እንደገለፀው፤ ፕረዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ እ.ኤ.አ በ1975 የኤርትራ ህዝቦች የነፃነት ግንባር በኃላም በ1994 የኤርትራ ህዝቦች የዴሞክራሲና የፍትህ ግንባር ሊቀ መንበር ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ ለስልጣን ካላቸው ከፍተኛ ጥማት የተነሳ ስልጣናቸውን ለመጠበቅ ሲሉ የተለያዩ ቴክኒኮችና ታክቲኮችን ይጠቀሙ እንደነበር ገልጿል፡፡

ከታክቲኮቹ መካከል በግንባሩ የነበሩ ምሁራን ታጋዮችን የማግለል፣የተለያዩ ተቀፅላዎችን የመለጠፍ፣ ለምሳሌም ጀርመን አገር ለተማረ ታጋይ ፣ንኡስ ከበርቴ፣ሶቬየት ዩኒየን ለተማረ ብረት፣ኢትየጵያ ለተማረ የአዲስ ልጅ ወዘተ የመሳሰሉ ቅፅል ስሞችን በመስጠት እና በእስራኤልና አሜሪካ አስተሳሰብ የተንሳፈፉ ንኡሳን ከበርቴዎች በማለት ሞራላቸው እና የትግል ወኔያቸው እንዲጎዳ በማድረግ ፣እነዚህ ምሁራን ታጋዮች ያልተማረውን ታጋይ ጥቅም የሚፃረር አስተሳሰብ እንደሚያራምዱ በማስመሰል የጥላቻ መንፈስ በመንዛት እንዲገለሉ እነዚህ ምሁራኑ የሚያራምዱት ማንኛውም ዓይነት ሀሳብ ተቀባይነት እንዳያገኝ በማሳደም እና የፕረዚደንት ኢሳያስን ሃሳብ የሚቃወሙትን ደግሞ ባቡር እንደቀደሙና ከሀዲድ እየወጡ እንደሆኑ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ የማካሄድ ተግባር እንደ ዋነኛ ታክቲክ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

እነዚህ ባቡር ቀደማችሁ የተባሉት ምሁራን የሚከተላቸው እጣ ፈንታም ግድያ ወይንም እስራት ሲሆን ግድያውና እስራቱ የሚከናወነው "ሰልፍ ለነፃነት" እየተባለ በሚጠራው ሚስጥራዊ ቡድን ሆኖ ቡድኑ 15 የፖለቲካ አባላት እና 30 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ጠቅላላው በ45 አባላት የሚመራና ተጠሪነቱ አሁን በእስር ቤት እየማቀቁ ለሚገኙት አቶ ጴጥሮስ ሰሎሞን ነበር፡፡ግድያው የሚፈፀመው በቀጥታ ሳይሆን በውጊያ ወይም በጠላት ሰላዮች እንደተገደሉ በማስመሰል ለታጋዩ ሃዘን በማወጅ ፣ ስለ ጀግንነታቸው በግጥምና መነባንብ እንዲገለፅ በማድረግና በሌሎች የማስመሰያ ዘዴዎች የግለሰቦቹ ሞት ሚስጢር ሆኖ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ከተገደሉት ብርቅየ ኤርትራውያን ምሁራን ታጋዮች መካከል

አብራሃም ተወልደ፣ ሙሴ ተስፋሚካኤል፣ዓይነ አለም የማነ እና ዓብደላ ዳውድ እንደ አብነት ይጠቀሳሉ። እዚህ ላይ አቶ ኢሳያስ ላልተማሩት ታጋዮች መወገናቸው ሳይሆን ተቃናቃኝ ለማጥፋት ብቻ እንደሆነና ላልተማሩት ታጋዮችም እረኛ፣ገበሬ፣ባላገር ፣ፀጉራም ጡንቻ ወዘተ የመሳሰሉ ቅፅሎችን በመለጠፍ ያንቋሽሹ እንደነበር ፒሎት ያብራራል።

ደርግ በሁሉም ግንባሮች ተከታታይ እና ኣሳፋሪ ሽንፈት ሲከናነብ እና ወደ መውደቅ ሲቃረብ አቶ ኢሳያስ ዴሞክራሲያዊ ፣ነፃ መንግስት ፣ነፃ ፕሬስ እና ሁሉም የኤርትራ ተቃዋሚ ሃይሎችን የሚያሳትፍ በህዝብ የተመረጠ መንግስት በኤርትራ እንደሚመሰረት የማታለያ ዲስኩራቸው ያስተላልፉ እንደነበሩ ፒሎት ይጠቅሳል። ፒሎት አያይዞም የአቶ ኢሳያስ ዲስኩር ለእርሳቸውን እና መሰሎቻቸው የነበረው ፋይዳ ሲተነትን አብዛኛውን ታጋይ ደርግን ከመጣልና ነፃነትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ዴሞክራሳዊ ሁኔታ ይፈጠራል ብሎ ይገምት ስለነበር ምናልባትም ዲስኩሩ እውነት የሚመስል ከሆነ በታጋዩ መካከል መረጋጋት ለመፍጠር ይረዳል ተብሎ እንደሆነ ያስቀምጣል። የነ አቶ ኢሳያስ ቡድን ድሮውንም ቢሆን ሳያውቁ አምልጧቸው ትግሉ በድል ይጠናቀቅ እንጂ ባቡር እንዴት እንደሚሰበር እናውቃለን ብለው የህዝብ ይሁንታ እንደማያስፈልጋቸው ድብቅ ዓላማ አንግበው ነበር።

ፕረዚዳንት ኢሳያስ ከድሮ ጀምረው በማደናገርና በቅጥፈት እንጂ ቁርጥ ያለ አቋም በማራመድና መከራከር አይታወቁም ይላል ፒሎት ።ለምሳሌ ዳዊት ወ/ጊርግስ ከተባለ የደርግ ባለስልጣን ጋር ከህዝባዊ ግንባር ማዕከላይ ኮሚቴ እና ፖሊት ቢሮ ዕውቅና ውጪ በደርግ በደል ለሚደርስባቸው ኤርትራውያን ይራራሉ በማለት በተደጋጋሚ በሚስጥር ሱዳን ውስጥ ይገናኙ እንደነበርና ደረግን አስመልክቶ የሚያዙት አቋምም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚዋዥቅ እንደነበር ያስቀምጣል። ለዚህ እንደ መገለጫ የሚያስቀምጠውም ህወሐት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደርግን ከስልጣን ማስወገድ የሚል ውሳኔ በጉባኤው ሲያስተላልፍ እነ አቶ ኢሳያስ ግን ደርግን ክደው ለሚመጡ የደርግ ወታደሮች ጥበቃ እናደርግላቸዋለን የሚል የቅጥፈት መልእክት ነበር ያስተላልፉ የነበሩት።እንደ ፒሎት አባባል የደርግ መንግስት በፌዴሬሽን መልክ ኤርትራን የማስተዳደር ስልጣን ለአቶ ኢሳያስ ቢሰጣቸው አይናቸውን አያሹም ነበር ይላል።

የደርግ ስርአት ተገርስሶ ኤርትራ ነፃነቷን ስትቀዳጅ አቶ ኢሳያስ “ሰልፍ ለነፃነት” የተባለውን ሚስጢራዊ አደረጃጀት አያስፈልግም በስብሷል፣ሚስጥራዊነቱ ከሽፏል ወዘተ ብለው አፍርሰዉታል። ድርጅቱ ያፈረሱበት ዋነኛ ምክንያት ግን ፕረዚዳንቱ በእኩይ ተግባራቸው ተፀፅተው ሳይሆን የአደረጃጀቱ ሚስጥራዊነት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር እንዲሆን በማሰብና የአደረጃጀቱን ስያሜ 72 በሚል በመቀየር ሚስጥራዊነቱ ከእሳቸው ጋር የጠበቀ ግኑኝነት ባላቸው እና በቀይ መታወቂያ በሚታወቁት

አካላት ዘንድ ብቻ እንዲታወቅ ፤ ስልጣናቸውን የሚቀናቀን ወይም የሚቃወም ከተገኘም ያለ ምህረት እንዲገደል ወይም እንዲታሰር በሚል የአቶ ኢሳያስ የግል ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ሆኖ እንዲያገለግል ነበር።

አቶ ኢሳያስ ነፃነቷን የተቀዳጀችውን አዲሲቷን ኤርተራ ሲመሩ በደርግ ውድቀት አከባቢ ይፅፉት እንደነበረው በሁሉም የኤርትራ ህዘቦች ዘንድ ይሁንታን አግኝተውና ፣የአለም አቀፍ ህግን አክብረው ለመግዛት ሳይሆን በጫካ አስተሳሰብ መምራታቸውን ነበር የቀጠሉበት።እንደ አገርና መንግስት በህግ እና በተጠያቂነት ሳይሆን የማፊያ አካሄድና የዜሮ ድምር አስተሳሰብ ውስጥ ተዘፍቀው ነበር አዲሲቷን አገር መምራት የተያያዙት። አገር ለመምራት ዝግጁ ካለመሆናቸውም በላይ ገና በጠዋቱ በኢትዮጵያና በሌሎች የጎረቤት አገሮች ጀርባ ላይ ተንጠልጥለው ታዝለው በህገ ወጥ መንገድ ኤርትራን የማሳደግ የዜሮ ድምር አቅጣጫ ይዘው ነበር የተንቀሳቀሱት።

አገር ተረክበው የኤርትራ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያማከለ የሽግግር መንግስት ከመመስረትና የኤርትራ ህዝብን ሉአላዊ የስልጣን ባለቤት ከማድረግ ፣የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብት የሚያስጠብቅ እና የመንግስትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ ህገ-መንግስት አርቅቆ ከማፀደቅ ይልቅ ህዝቡን "የእስራኤል ተሞክሮ " በማለት ማደናገር ነበር የተያያዙት።እዚህ ላይ እስራኤል አንድ አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ያላት፣እንደ ሀገር ከተመሰረተችበት ጊዜ አንፃር ሲታይም አጭር ታሪክ ያላት ሆና፣ቢኢኮኖሚ፣በቴክኖሎጂ እና እጅግ የሰለጠነ የወታደራዊ ኃይል ባለቤት የሆነች አገር እንደመሆኗ አገሪቱን እንደ ሞደል መውሰድ በመሰረቱ ስህተት አይሆንም።

ስህተት የሚሆነው ከህዝብ ጥያቄ ለመሸሽና በተለመደው ቅጥፈት ለመደለል ሲደረግ ብቻ ነው። የአቶ ኢሳያስ አስተሳሰብም ኤርትራን እንደ እስራኤል ለማበልፀግና የኤርትራ ህዝብን ኑሮ ለማሻሻል ሳይሆን ካላቸው የማፊያ አካሄድ እና የዘቀጠ የዜሮ ድምር አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው።የአቶ ኢሳያስ የማፊያ አካሄድ እና የዜሮ ድምር አስተሳሰብ እውን የሚሆነውም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደራዊ ተቋም በመገንባትና የአፍሪካ ቀንድ ጎረምሳ በመሆን ሁሉንም ጎረቤቶቻቸውን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው የሚፈልጉትን ማንኛውም ጥቅም ከቻሉ በውዴታ ካልቻሉም በጉልበት ለማስፈፀም የሚያስችሏቸውን ታክቲኮችን መጠቀም መሆኑን ገና ከጠዋቱ መርህ አድርገው ይዘውታል። ከነዚህ ቴክኒኮች አንዱ "ሳዋ" የተባለ ወታደራዊ ማሰልጠኛ በመመስረት የኤርትራ ህዝብ ገና የሰላም አየር በደንብ ሳያጣጥም እ.ኤ.አ በ1995 አስራ ስምንት ዓመት የሞላቸውን ወጣቶች ፆታ ሳይለይ በግድ ኅትተው ወታደራዊ አግልግሎት እንዲሰጡ አድርገዋል። አቶ ኢሳያስ ይህንን ሲወስኑ የትኞቹንም ሹማምንቶቻቸውን አማክረው ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ነበር ይላል የውስጥ አዋቂ የSallina.com እንግዳ ፒሎት። ወታደራዊ አገልግሎቱ ጥሩ ተሞኩሮ ሆኖ የኤርትራ ህዝብን ህይወት የሚቀይር ሳይሆን የወጣት ኤርትራውያንን ህይወት የሚቀጥፍ እና ለባርነት የሚዳርግ ሆኖ እስከ ዛሬ ድረስ በማገልገል ይገኛል።

የሲንጋፖር ተሞኩሮም ልክ እንደ እስራኤል ተሞኩሮ የኤርትራ ህዝብን ህይወት ሳይቀይር የወጣቶቹ ወታደራዊ አገልግሎት  የእድሜ ልክ የባርነት ዘመን እንዲሆን አድርጎታል። አቶ ኢሳያስ “ሓዳስ ኤርትራ” በተባለች ብቸኛ ጋዜጣ ስለ ሲንጋፖር  ሲደሰኩሩ  በጣም የሰለጠነች ፣ አጠቃላይ ህዝቧ በከተማ የሚኖርና መካከለኛ ገቢ ያለው በመሆኑ ኤርትራም ይህንን  ተሞኩሮ ሳታላምጥ መቀበል ይኖርባታል ይሉ ነበር። በተጨባጭ ሲታይ ግን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የኤርትራ ህዝብ በ30 ዓመታት የፀረ-ደርግ ትግል የጎበጠው ወገቡ ሳይቃና እና የልጆቹ መስዋእትነት መልካም ፍሬ ሳያፈራ ዳግም ከደርግ ጭቆናና ግፍ የባሰ የመከራ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ይገኛል።

ኤርትራ እንደ አገር ከተቋቋመች እና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዘንድ እውቅና ካገኘች በኃላ የራስዋ ገንዘብና የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖራት ግድ ስለነበር  አሁን በስራ ላይ ያለውን  ናቅፋ የተሰኘ የመገባቢያ ገንዘብ  እ.ኤ.አ ኖቬምበር 8 ቀን 1997 አትማለች። ኤርትራ የራሷን ገንዘብ ስታሳትም በመሪዎቿ ዘንድ ከጎረቤት አገራት ጋር  ስለሚኖራት የገንዘብ የቁጥጥር ስርዓት መልክ እንዲይዝ በማስብ እንዲሁም ፣በዓለም አቀፍ የገበያ ህግጋትና የመገባያያ ስርዓት በማመን ያደረጉት እንዳልነበር ለመረዳት ይቻላል ። በዚህም የአንድን ሉአላዊ አገር ፤የኢትዮጵያን የገንዘብ ቁጥጥር ስርዓት  እንደ ፈለጉ  የማስተዳደር አዝማሚያ በአቶ ኢሳያስ ዘንድ ገኖ ይታይ ነበር። ይሁን እንጂ አቶ ኢሳያስ ያልጠበቁት አንድ ነገር ተከሰተ ! የኢትዮጵያ መንግስት የራሱን አዲስ ገንዘብ አሳተመ ፣ የአቶ ኢሳያስ አንድ ናቅፋ በአንድ የኢትዮጵያ ብር ለውጥ ወይም ብርና ናቅፋ እኩል ዋጋ እንዲኖራቸው የሚለው የኤርትራ መንግስት አስተሳሰብም በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀረ። ኢትዮጵያ እና ኤርትራ ሁለት የተለያዩ ሉአላዊ አገሮች እንደ መሆናቸው መጠን በመካከላቸው ሊኖር የሚገባው የንግድና የገበያ ስርዓት አለም አቀፍ ህግን የጠበቀ መሆን እንዳለበት በኢትዮጵያ በኩል ይፋ ተደረገ ። አቶ ኢሳያስ ሊቀበሉት ባይችሉም ። ይባስ  ብሎም የኤርትራ ዲፕሎማቶችም ሆኑ ነጋዴዎች የኢትዮጵያን ደህንነትና  ጥቅም ለአደጋ በሚያጋልጡ የተለያዩ ህገወጥ ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ  ወደ ማድረግ ህገ ወጥ ድርጊት ተሸጋገሩ።

የአቶ ኢሳያስ መንግስት ዲፕሎማቶች  አዲስ አበባ ቁጭ ብለው ስለ ሁለቱ አገራት  መልካም ግንኙነት ሲሰሩ እንዳልነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይልቁንስ በህገ ወጥ  መንገድ  ዶላር ሲሰበስቡ፣ ኮንትሮባንድ እና ሌሎች ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን ሲተገብሩ እንጂ።አሁንም ቢሆን የኤርትራ ዲፕሎማቶች በሄዱበት አገር   በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ፣ኮንትሮባንድ፣ህገውጥ የገንዘብ ዝውውር ወዘተ በመሳሰሉት ህገ-ወጥ ተግባራት እንደተሰማሩ የተባበሩት መንግስታት የሶማሊያ እና ኤርትራ የቁጥጥር ቡድን  ባወጣው ሪፖርት ይፋ አድርጎታል።

አቶ ኢሳያስ  በህገ-ወጥ ተግባር ተጠምደው የኢትዮጵያን ህዝብና መንግስት ደህንነትና ጥቅም ያለገደብ እየጎዱ ማየት ተገቢ ስላልነበር የኢትዮጵያ መንግስት በሁለቱ አገሮች  መሀከል ያለው የንግድ ግንኙነት

ስርአት ባለው መልኩ መመራት እንደሚኖርበትና ትልቅ መጠን ያላቸው ሸቀጦችን በየትኛውም ዓለም እንደሚደረገው በኤልሲ (Letter credit) እንዲከናወን ፤በሁለቱ ሀገራት ድንበር መካከል ለፍጆታ የሚውሉ ሸቀጦች በአነስተኛ መጠን ማለትም አንድ ነጋዴ ከ2500 ብር ያልበለጠ ዋጋ ያላቸውን ሸቀጦች ብቻ እንዲያስተላልፍ መወሰኑን ተከትሎ ኤርትራ ላይ ምግብ ነክ ሸቀጦች ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ኣሳዩ እናም አቶ ኢሳያስ ታዝሎውበት ከነበሩበት የኢትዮጵያ ጀርባ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዲወርዱ ተደረገ።

አገራችን የሁለቱን ሀገሮች ድንበር በተመለከተ ያልተፈቱ ችግሮች መኖራቸውን ብታውቅም እነዚህ ጉዳዮች በሰላም እና በድርድር መፈታት አለባቸው በሚል ትክክለኛ አስተተሳሰብ የመነጨ ጄነራል ስብሓት ኤፍሬም፣ አቶ የማነ ገ/አብ(ማንኪ)እና አቶ አብራሃ ካሳ የተባሉት የኤርትራ ባለስልጣናት ወደ አዲስ አበባ በመጋበዝ ከኢትዮጵያ ባለ ስልጣናትን ጋር ምክክር እየተካሄደ በሚገኝበት ሰዓት ነው አቶ ኢሳያስ ወረራውን እ.ኤ.አ ግንቦት 1998 ኢትዮጵያ ላይ የፈፀሙት። ሁሉም ነግር በጉልበት መፈፀም ይቻላል በሚል ፖሊሲያቸው የሚታወቁት ፕረዚዳንት ኢሳያስ ያራመዱት ፍልስፍናም በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ዘንድ ተቀባይነት በማጣቱ ያለአንዳች የድንበር ምክንያት የኢትዮጵያን ሉአላዊ መሬት ግፍና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን ወረው ያዙት።

የዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታም 34 የሚሆኑ የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶችን ያሳተፈው የሽግግር ጊዜ በድል ተጠናቆ በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ይሁንታ ያገኘ ህገ -መንግስት ፀድቆና የኢትዮጵያ ህዝቦች ከጭቆና ቀንበር ተላቀው ለዘመናት ሲናፍቁት የነበረው የልማት ጥያቄያቸው እውን በመሆኑ የተለያዩ ልማታዊ እንቅስቃሴዎችን እያከናውኑ ይገኙ ነበር። ነገር ግን በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት መሰረት ህብረ ብሔራዊ ይዘት እና ስብጥር ያለው ሰራዊት ለመመስረት ሲባል ደርግን ለመጣል ሲዋጋ የነበረው የኢህአዴግ ሰራዊት በጣም ከፍተኛ በሚባል ቁጥር በመቀነሱ፣በዛን ጊዜ የነበረው አነስተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊትም ቢሆን በምእራብና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል የነበሩ የፀጥታ ችግሮችን በማረጋጋትና በመጠበቅ የተጠመደ ስለነበርና ወረራው ከተፈጸመበት ትግራይና ዓፋር አከባቢ ከፍተኛ ርቀት ያለው መሆኑ ፣ በሌላ በኩል በትግራይ አነስተኛ የመከላከያ ሀይል ብቻ መኖሩን እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ያለአንዳች ተከላካይ ኢትዮጵያን መውረር እንደ ሚችሉ እና ፍለጎታቸውን በጉልበት እንደሚያሳኩ በማመን ወረራው ተፈፅሟል።

አቶ ኢሳያስ የኢትዮጵያ ህዝብን የአትንኩኝ ባይነት በቅጡ ሳያጤኑ የገቡበት ረመጥ በደንብ አርጎ ሲገርፋቸው በአፍሪካ ሕብረት፣በአውሮፓ ህብረትና በተባበሩት መንግስታት አማካኝነት ችግሩ በሰላማዊ መንገድና በድርድር እንዲፈታ ሲጠየቁ አሻፈረኝ ያላሉትን ያህል በጦርነቱ አሳፋሪ ሽንፈት ከገጠማቸው እና ከፍተኛ ለሆነ የህይወትና የንብረት ውድመት ምክንያት ከሆኑ በኃላ ሳይወዱ በግድ አልጀርስ ላይ የሰላም ስምምነት መፈረማቸውን ይታወሳል። የድንበር ውሳኔው ፍትሃዊነት የጎደለው ቢሆንም እንኳን

ለአቶ ኢሳያስ ጊዜያዊ ማስተንፈሻ መሆን ችሏል፡፡ ምክንያቱም ፍላጎትን በሀይል የመጫን ፖሊሲ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ላይደገም ቢሰበርም አቶ ኢሳያስ ግን  የአጭርና የረዥም ጊዜ በድንበር ውሳኔ የመንጠላጠል እድል አስገኝቶላቸዋል፡፡

አቶ ኢሳያስ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ላይ ፍላጎታቸውን በሀይል የመጫን ፖሊሲያቸው ቢከሽፍባቸውም ወረራውን ሲፈፅሙ ያልጠበቁትን ውጤት ግን አግኝተዋል፡፡ ፕረዚዳንቱ በአንድ በኩል ኢትዮጵያ ላይ ዳግም ወረራ መፈፀም የህይወታቸው  ፍፃሜ ሊሆን እንደሚችል በቅጡ እንዲገባቸው አድርጓል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ ህዝብን በስጋት ክልል ውስጥ  በማጠር ያለህገ-መንግስት እና ምርጫ  ፍፁም በሆነ አምባገነናዊ ስርአት እንዲማቅቅ በማድረግ የስልጣን ዘመናቸው እዲራዘም አድርጓል፡፡

አቶ ኢሳያስ ኢትዮጵያን በቀጥታ መውረር እንደማይችሉ በቂ ትምህርት ማግኘታቸውን ተከትሎ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ህዝብ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ትሩፋትን ማጣጣም ከጀመረ የኤርትራ ህዝብም ተመሳሳይ ጥያቄ ማንሳቱ ስለማይቀር ኢትዮጵያን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማተራመስ የሰላም እና ልማት ሂደቱ እንዲደናቀፍ እና ኢትዮጵያን የማዳከም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኤርተራን ህዝብ አማራጮችን አሻግሮ የማየት ዕድሉ በመዝጋት የአገር ሉዐላዊነት በመከላከልና ነፃነትን በማስጠበቅ ፕሮፖጋንዳ  ተሸፍኖ አቶ ኢሳያስ እድሜ ልካቸውን ያለ ህዝብ ይሁንታ በስልጣን የመኖር ፖሊሲያቸውን ለመተግበር እንዲሁም  ከሁሉም የኤርትራ ጎረቤቶች ጋር እንደ እብድ ውሻ እንዲናከሱ አድርጓቸዋል፡፡

የኤርትራ ህዝብ በከፈለው መራራ መስዋእትነት አማካኝነት በሀገሪቱ ነፃነት ፣ ሰላም፣ልማት እና ዴሞክራሲ ሊረጋገጥ ይችላል  የሚል ግምት በአብዛኛው ታጋይ፣በህብረተሰቡ እና በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ይስተጋባ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ፅድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ እንደሚባለው የኤርትራ ህዝብ  ሲናፍቀውና ሲጓጓለት የነበረው ነፃነት እንደ ጉም በኖ ከመቅረቱም በላይ ለተለያየ ጭቆናና አፈና ተዳርጓል፡፡ Reporters Without Borders የተሰኘው ቡድን እንዳለው  በአቶ ሲሳያስ አመራር የምትመራው ኤርትራ ወደ ትልቅ ወኽኒ ቤት ተቀይራለች፡፡ ጋዜጠኞች፣የመንግስት ባለስላጣናት የነበሩ ነባር ታጋዮች ፣የሃያማኖት መሪዎች እና ሌሎች ንፁሃን ዜጎች ያለምንም ፍርድ በ314 የሚስጥር ወኽኒቤቶች 229  ጫማ ያህል (69.8 ሜትር) ከባህር ወለል በታች እና 140 ዲግሪ በሚደርስ ከፍተኛ ሙቀት በኮንቴነር ውስጥ ፤አንዳንዶቹ እጅና እግራቸው ታስረው ፣ሌሎች ደግሞ ቁልቁል ተዘቅዝቀውና እጅና እግራቸው ከእንጨትና ብረት ጋር ታስሮ በአሰቃቂ እና ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ  ለህልፈተ ህይወትና ለከፍተኛ የጤና ቀውስ እንደተዳረጉ ገልጿል፡፡

የኤርትራ ዜጎች የአቶ ኢሳያስን ጭካኔና አረመኔነት መሸከም አቅቷቸው ፣በመኖርና በመሞት መሀከል ያለው ልዩነት ብዙም ስላልተራራቀባቸው ስደት ህይወትን ለማቆየት "Leave to live." የሚል መፈክር አንግበው እና የሞትን ህይወትን መሳ እድል ተጠቅመው ድንበር በማቋረጥ ወላጅ ዘመዶቻቸውን ጥለው በመውጣት ላይ ይገኛሉ።በዚህ መሰረት ከአጠቃላይ የኤርትራ ህዝብ ብዛት 25% ባለፉት 20 አመታት አገራቸው ጥለው እንደወጡ ቡድኑ አረጋግጧል። ይህ አሃዝ የሚያካትተው ሳይገደል ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ሳይቆስል ድንበሩን ማቋረጥ የቻለውን ብቻ መሆኑን ማስተዋል ይኖርብናል።ምክንያቱም እነዚህ ጭቆናና ባርነት አንገሽግሻዋቸውና ድንበር አቋርጠው የሚሄዱት ዜጎች በአቶ ኢሳያስ አባባል "ከሃዲዎች"በመሆናቸው ድንበር ሲያቋርጡ ከተገኙ ያለምህረት እንዲገደሉ ትእዛዝ ከተሰጠ ውሎ አድሯል እና ይህ አሀዝ ድንበር በማቋረጣቸው ምክንያት ህይወታቸው ያለፈውን፣ ለከፍተኛ የአካል መጉደል የተዳረጉትን እና በእስር ቤት እየማቀቁ የሚገኙትን አያካትትም።

የተባበሩት መንግስታት የኤርትራ እና የሶማሊያ የቁጥጥር ቡድን እንደገለፃው የእነዚህ ድንበር አቋርጠው የሚሸሹት ዜጎች ቤተሰቦች 50ሺ ናቅፋ (3333 ዩኤስ ዶላር) እንዲከፍሉ ወይም ያለ ገደብ እንዲታሰሩ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ያስገድዳል። በሌላ በኩል ደግሞ የአቶ ኢሳያስ የጦር መኮንኖች የገዛ ዜጎቻቸውን በማሳደድ በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተሰማርተው ኤርትራን ጥለው መውጣት የሚፈልጉ ዜጎችን በመመልመል ከእያንዳንዱ ድንበር ተሻጋሪ ዜጋ 3ሺ የአሜሪካ ዶላር ይቀበላሉ።የኤርትራን ድንበር ከተሻገሩ በኃላ ከሱዳን እና ግብፅ ወደ እስራኤል ወይም አውሮፓ ለማንንዝ እስከ 20ሺ የአሜሪካ ዶላር እንሚያስከፍሉ እና የተሰበሰበውን ገንዘብም በስዊዘርላንድ የኤርትራ ኤምባሲ ሰራተኛ ስም ወደ ስዊዝ ባንክ እንደሚገባ የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ቡድን ባገኛው የባንክ ሂሳብ ማረጋገጥ ችሏል። ይህንን ገንዘብ መክፈል ለማይችሉ ወገኖች ደግሞ ከሌሎች ህገ ወጦች ጋር በመተባበር በሲናይ በረሃ ከውስጥ ሰውነታቸው አካላት መሀከል ኩላሊታቸውን በመውሰድ ፣መደብደብ እና በሴቶች ላይ ወሲባዊ ጥቃት መፈፀም ወዘተ አሰቃቂ ድርጊቶች ምክንያት ብዙዎቹ ለህልፈተ ህይወት፣ለከፋ ህመም እና ለአእምሮ መቃወስ እንደሚዳረጉ አረጋግጧል።

የአቶ ኢሳያስ መንግስት "የአገሪቱን አንድነትና ህልውና በማስጠበቅ" ስም የነበረችውን አንዲት ዩኒቨርሲቲ በመዝጋት ማንኛውም 18 ዓመት የሞላው የኤርትራ ወጣት ነፃ ወታደራዊ አገልግሎት እና ወታደራዊ ኢንዶክትሪኔሽን ከትምህርት ጋር ተዳብሎ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ምንም እንኳን የወታደራዊው አገልግሎት ዘመን18 ወራት ነው ቢባልም የኤርትራ ወጣቶች የህይወት ዘመናቸውን በሙሉ በባርነት ቀንበር ታስረው ያለምንም ተስፋ በጨለማ እንደሚያሳልፉት እና አንስት ምልመሎች ደግሞ በተለያዩ የጦር መኮንኖች የከፋ ወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አጣሪ ቡድኑ አረጋግጧል።

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት በእብሪት የተወረረውን ዳርድንበሩን በሃይል ካስከበሩ በኃላ የአቶ ኢሳያስን ትንኮሳ ለልማታችን ስንል እንታገስ  በሚል መርህ ሀገራችን  ድንበር አልፈው ችግር የሚፈጥሩ የኤርትራ ሃይሎችንና ተላላኪዎቻቸውን በመከላከል ልማቷን ስታከናውን ቆይታለች፡፡ይሁን እንጂ  የአቶ ኢሳያስ እብሪት ወደ ሽብርተኝነት በመሸጋገሩ ኢትዮጵያን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማተራመስ ስትራቴጂ በመከተል አያሌ የህይወትና የንብረት ጉዳት በኢትዮጵያ ላይ አድርሷል፡፡በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ራስን የመከላከል የፖሊሲ ለውጥ በማድረጉ የአቶ ኢሳያስ ወታደሮችም ሆኑ ተላላኪዎቻቸው ለሚያደርሱት ጥቃት ተመጣጣኝ አፀፋዊ  ምላሽ በመስጠት አቶ ኢሳያስ የቁስላቸውን ህመም ዋጥ እንዲያደረጉት ማድረግ ተችሏል፡፡

የአቶ ኢሳያስ የትርምስ ፖሊሲ ከኢትዮጵያ አልፎ  ለሁሉም ጎረቤት አገሮችም ተርፏል፡፡የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታ ጥበቃው ም/ቤት የኤርትራ መንግስት አፍሪካ ቀንድን በማተራመሱ ሁለት ተከታታይ ማዕቀቦችን ጥሎበታል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የኤርትራ መንግስት በኣለም አቀፍ ማህበረስብ ዘንድ የተተፋ መንግስት ሆኗል፡፡

የኤርትራ ህዝብ ከዚህ የጨለማ ኑሮ እንዲላቀቅ የአለም ማህበረሰብ እያደረገ ያለው ሚና አነስተኛ ነው፡፡ ቢሆንም ረፈደ እንጂ አልመሸም ፡፡ስለዚህ የኤርትራ ህዝብ ነፃነት የሚረጋገጠው በራሱ በኤርትራ ህዝብ ቢሆንም እንኳን ለ50 ዓመታት ያህል በጭቆና ቀንበር የማቀቀን ህዝብ የማገዝና የመርዳት የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን የሞራል ግዴታ ነው፡፡